# የቁራ ጩኸት!

## "ትንሽ ግጥም… "

ወንድወሰን በየነ
ጥቅምት 2007 ዓ.ም.

# ምስጋና

«ሁሉ በእርሱ ሆነ።» እንዲል

ከነገሮች ሁሉ በላይ! የበጎች ባለፀጋ፣ የጥበብና የተዓምራት ባለቤት፣ የምህረትም አባት የሆነው ኃያሉ እና ቸሩ ፈጣሪ ዓምላክ ሕያው እግዚአብሔር እጅግ ላቅ ያለ ልባዊ ክብርና ምሥጋና ይግባው። አሜን!

እንዲሁም በእርሱ ፈቃድ ረዳት ደጋፊ ለሆኑኝ ቤተሰቦቼ፦

> አክስቴ ወ/ሮ ሙሉእመቤት ገ/ዮሐንስ እና
> እህቴ ወ/ሮ ሒሩት በየነ
> ከማይነጥፈው የሃሳብ ድጋፋቸው ሃሻገር የህትመቱን ሙሉ ወጪ በመሸፈናቸው፣

> የአጐቴ ባለቤት ወ/ሮ የምሥራች ጥላሁን
> ከማበረታታትም በላይ በኮምፒዩተር ትየባውና ተደጋጋሚ እርማቱ አንዳች ሳትሰለች ብርቱ ሙያዊ እገዛ በማድረግ ጭምር ስለረዳችኝ፣

> አጐቴ አቶ ጌታቸው ገ/ዮሐንስ
> ዝንባሌዬን ካወቀበት አንስቶ ልዩ የሃሳብ ድጋፍና ማበረታቻው ስላልተለየኝ፣

> የአጐቴ ልጅ ወ/ሪት ፂዮን ጌታቸው
> የሽፋን ዲዛይኑን በማዘጋጀት ረገድ ላሳየችው ትጋት፣

> ነዋሪነታቸው በአሜሪካ ሃገር ዳላስ የሆኑት የአክስቴ ልጆች ወ/ሪት ማኅሌት አራርሶ (ሲ.ሲ.) እና ወ/ሪት ሐዊ አራርሶ እንዲሁም ወዳጄ ወጣት ዳዊት አስፋወሰን ከሞራል ድጋፍ

ጋር ማነቃቂያ ነገር ሸጉጥ በማድረግ ጭምር ስላበረታቱኝ፤ውለታ ቀጣሪው ፈጣሪ ዓምላክ ከእነወዳጅ ቤተሰቦቻቸው ሙሉ ጤንነት፣ የተባረከ ሕይወትና የተቃና ኑሮ ያጐናፅፋቸው ዘንድ ከልብ እየተመኘሁ፤ እጅግ ከፍ ያለ ምሥጋናዬን ከአክብሮት ጋር አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ለረጅም ጊዜያት ከሃሳባቸው ሳይለዩኝ፣ በችግር ወቅትም ኪሳቸውን በመዳበስ ጭምር ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ በመስጠት እና መልካም ነገር በመጠበቅ ተስፋ ሳይቆርጡ ላበረታቱኝ ወዳጆቼ፡-

አቶ ገሞራው ካሣ፣ አቶ ወንድወሰን ተሸመ፣ አቶ ፀጋዬ ፈጤ

አቶ አስፋው ኃይሉ፣ አቶ ጁሃር ሙሣና ባለቤቱ ወ/ሮ መሠረት አቶ እስራኤል ጌታቸውና ባለቤቱ ወ/ሮ አብነት ጌታሁን አቶ ሁመድ ኢብራሂም፣ አቶ ዓለማየሁ እሸቱ (ቾምቤ) እና ባለቤቱ ወ/ሮ ሙሉእመቤት አበራ እንዲሁም ሁሉን መዘርዘር ባለመመቸቱ ምክንያት በስም ያልተጠቀሳችሁ ወዳጆቼንና የሙያ አጋሮቼን በሙሉ እግዚአብሔር በውለታው ያስባችሁ ዘንድ እየተመኘሁ፤ ከልብ የመነጨ ትኁት ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ እላለሁ፡፡

> ማስታወሻነቱ ደግሞ ለእናቱ ለወ/ሮ ምንትዋብ ገ/ፃድቅን ወ/ማርያም ይሁንልኝ፡፡

# መታሰቢያነቱ

> ለተሾመ በቀለ ወ/ጊዮርጊስ

> ለአብነት በቀለ ዋቅቶላ

> ለሙሴ በፍቃዱ ወ/ጊዮርጊስ

> ለሰሎሞን አንለይ እና ለአበራ ኃይሉ ይሁንልኝ፡፡

ቸሩ ፈጣሪ ዓምላክ የደጋግ ሰዎችን ነፍሳት ይማርልን፡፡ ለዘለዓለምም በመንግሥተ ሰማያቱ ያኑርልን፡፡

> ወዳጄ ወጣት ሰሎሞን አንለይ፤

ይህ ጽሑፍ ታትሞ ለማየት ከማናችንም በላይ እንደጓጓህና እንደናፈቅህ ነገር ግን የጊዜ ጉዳይ ሆነና ምኞት ተስፋህ ሳይሞላ ፋታ በማይሰጥ ድንገተኛ ህመም በመነጠቅህ መሪር ኀዘኔ እጥፍ ድርብ ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ እግዚአብሔር ፈቅዶ ምርጥ ግጥሞችህ ለንባብ እንዲበቁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

# ማውጫ


ገጽ

እንደ መቅድም ....................

(ልምድ እንቀስምበት) .................... 1

መግቢያ .................... 2

ምሥጋና .................... 4

ዕድል .................... 5

ኑሮና ውሳኔ .................... 6

እምነት .................... 7

ከቶስ - ማን! .................... 7

ሰው ሳልጠላ .................... 8

ጫና! .................... 8

መኝታና ንቃት .................... 9

ሐሳብ .................... 9

ናፍቆት .................... 10

ጉስቁልና .................... 11

የሸንብራ ጥላ ስር ፍርድ .................... 12

የምኞች ዓለም .................... 13

ለራስ ነው ማልቀስ .................... 14

ፍርጃ! .................... 15

የሚመክ! .................... 15

የዘመን ሞገሶች .................... 16

ወዳጅን አጣኋት .................... 17

ጊዜ .................... 18

ሰው .................... 19

ጀበና ግዝፈቱ .................... 20

ሞት - አይወደድምም አይፈራምም! .................... 22

አስተውለው ደረጃውን .................... 23

ለካንስ ይሞታል!? .................... 24

ልብ እንጂ አሚፋለም ... .................... 25

«ነፍሱን የወደደ?...» .................... 27

አዘኸርበት ነፍሴን .................... 28

ግራ ወዳጅነት - ግር ደመኝነት! .................... 29

አትጨነቅ! አስብ .................... 31

አታንጋጥ!... .................... 32

ሕልም አለኝ! .................... 34

ያንዴ ፈረቃ .................... 36

ንጣት ሲኸርጉረጉር! ሲጠቆር .................... 38

የቁራ ጩኸት! .................... 40

«የውጭ አልጋ» .................... 43

ገራገሩ .................... 45

የውድቅት አናብስት! .................... 48

የብረት ዘንዶ ጉያ! .................... 54

ያ - ጥቁር ግሥላ!

(ቁጥር - 1) .................... 62

## ዕድል

ወፌ! ውሽም_ውሽሞ እንደ.ት ነሽ!?
እቴ - እናቴ፤ አለሽ ወይ - በነፍስሽ
ነኝ እኔስ አሳቢሽ፣ ናፋቂሽ!
እንጉቻ እራሪ - ከማይሽ
ከዕድል ብራሪሽ ---- 'ልዋስሽ!
ግና ሲመኛሽ እንኳ ሲመኛሽ
እስኪ ባገኝሽ።
አግኝቼሽ!
ደርሼ አይቼሽ - ነገርሽ
እወንዜ ዳርሽ ብቃይሽ
የሁለመናዬን! - ባዋይሽ።

መጋቢት - 1984 ዓ.ም.
ዐሰበ - ተፈሪ (ጭር)

* በጣም ስለሚወዳት ለአብሮ አደግ ጓደኛዬ
ለፀጋዬ ፈጡ ማስታወሻ ስጦታዬ ትሁን።



## ኑሮና ውሳኔ

ፍጊያ! .... ሽር -- ጉድ!
ጉድ ጉድ
ላይ -- ታች፣ ውጣ - ውረድ
የሻረው - ሻረው ግሳት
መጣት - ፍርድ!
የሕይወት ቧልት፤
ቀሊል ተዋዕዖ ትርፋ - ትርፍ
ትንቅንቅ! ነፍስያ፤
አበቅየለሽ - ሽንፈትየለሽ ጭፍጭፍ!!
ኑሮና ውሳኔ
የመጫረስ ጠኔ።

ሰኔ - 1984 ዓ.ም.
ዐሰበ - ተፈሪ (ጭር)

* ስለ አግርሞት - ውዴታቸው
ለወዳጆቼ ለአቶ ሽመልስ ሹምዬና
ለመምህር መስፍን በተሴ ጀባ ብያቸዋለሁ።

## እምነት

እምነት - - - - እምነት
ለነፍስ ያሉት እምነት!
ፍሁም የልብ ነው --- ልቡም የጌታ ቤት።
የማያናውጡት የእውነት መሠረት!
የፍቅር መፍለቂያ! መንቆርቆሪያ ጅረት።
አይጠገብ ፀጋ! የፅኑ ተስፋ ግት።
በቅንነት ወኔ! በምህረት እንጀት
ፈተናን ተጋፍጠው -- የታገሡት ጉዳት!
በአብሮ መኖር ጥበብ፣ በማስተዋል ኅብረት
ፍስሐን ተቋድሰው -- ያጣጣሙት ሕይወት።
እምነት፣ እምነት! ዋ - - - - እምነት!!

ሰኔ - 1984 ዓ.ም.
ሀሰበ ተፈሪ (ጭሮ)

## ከቶስ - ማ?

እኔ - - - - ድህነቴን
ድህነቴም - - - - እኔን፤
ባንጣገብ እንጂ
ባንማረር እንጂ
ከቶ ማ— ሊለየን?!
እውነት ሽፍጥ ላታውቅ
(አታውቅምም!)
ዝንተ - ዓለም ... ሕያው ነን!
አብረን ነን! አብረን ነን።
ከላስ!

ሰኔ - 1984 ዓ.ም.
ሀሰበ ተፈሪ (ጭሮ)

* በረባ ባልረባው ከራሱ ጋር እየተጣላ - እየተባላ!
እንዲኖር ለተገደደው ለሰብዓዊው ፍጡር - «እንደራሴዎች»።



## ሰው ላልጠላ!

ቃል ገባሁ - በተስፋ
ቢከፋም - የከፋ!
የሚከብድ ጫና - ዳፋ።
ነፍሴም ቢሆን ተንጠልጥላ!
ዝንተ - ፍሬን፣ ሰው ላልጠላ።

ሰኔ - 1984 ዓ.ም.
ሀሰበ - ተፈሪ (ጭሮ)

መታሰቢያነቷ፡- ለአባቴ ለአቶ በየነ ይመኔ ይሁንልኝ።
ዕድሜ ልኩን ሳይታክት! የፍልስፍና ያህል መመሪያው
አድርጎት ሽክም አደራውን ጭኖብኝ አልፏልና።

## ጫና

ሁዳድ ሙሉ ሙሉ! ቡቃያ ተኝቷል
ሠንበሌጡ እንሷቸው
ቁጤማው እንሷቸው
ግጦሹ ያልበቃቸው! ከብት ይነዱበታል!!
ምድሪቱም አትነቃ፣ ጫና ወዶላታል
ምነኛ ልባሞች!
ምነኛ ደፋሮች - ጨክነውባታል!?

ሐምሌ - 1984 ዓ.ም.
ሐረር

## መኝታና ንቃት

ጥንትም . . . . ይባል አይደል?
«የበዛ መኝታ - ድህነት ይጠራል»
ታታሪስ ማልዶ ይነቃል!
ከፉ ቀን ሲያጠቃ
የተኛ ይተኛ! የነቃም - ይነቃ!

ነሐሴ - 1984 ዓ.ም.
ሐረር

## ሐሳብ

ልቡናዬ፤ ርቀት ጥልቀቱን ያስባል!
ምኞት ቀልቤም እንጂ ተነስትዋል
ከወዴት እንዲደርሱም እንጃ?!
የየብቻ ብቻ ሩጫ
ወይ - 'ድሎት፣ ወይ' - ፍርጃ!?

ነሐሴ - 1984 ዓ.ም.
ሐረር



## ናፍቆት

የእኔስ ናፍቆት - ሁለቴ!
አንዱ - እኋላ - ኋላዬ
ሌላው - እፊት እፊቴ::
እወይ! መንከራተት!
እወይ! - መጓጓቴ!?
ምፀአት! ናፍቄ
ከንቱ መዋተቴ::

ነሐሴ - 1984 ዓ.ም.
ሐረር

* ሁሉም ግርም ይሰኝበት ስለነበረ በእውነት ቀኝ እጅ ወዳጄን ወጣት ሰሎሞን አንለይን ያውሳልኝ::

## ጉስቁልና

እዩት፣ እዩት - እማ!
እዩት ጉዱን! ጉስቁልና
በለሆሳስ ሲያንሾካሾክ፣
ሲያሜውተን! ዋዛ - ዋዛ
ሲያሽ - ሲላፋን
ሲተሻሸን! መና - መና
ሲጓተት - ሲጐናተል
ሲያጓጉለን! በየፊና::
ላመሉ፣ ደረሶ ያፍቅሮቱን
ወዶልን!
የኛ - እኛይቱን፣
ቁርበት ብጤ ወና
ሙጥኝ - ቁርኝት! ዝምድና።
ከአች አምና፣
አቻም የለውና - የእንዳምና!
ከድሮ - ኑሮ - ንሮ!!
ወደር የለውምና – የዘንድሮ!!

ነሐሴ - 1984 ዓ.ም.
ሐረር



## የሽምብራ ጥላ ሥር ፍርድ!

የሩቅ ዘመን ብሂል፣ የሩቅ ጊዜ ትዕንቢት
ጥንተ - ቅሪት እርሾ፣ ቃለ - ነቢብ ንግርት፤
ፍፃሜ - ዓለም እንኳ፣ ከተፍ ቢል ድንገት!
አይጥም - አይጠላ፣ ኹነቱ አይገመት።
ሁኖ እንጂ ነገሩ፣ ለመከራ ትውልድ
አቃቂር ፈተናው፣ ዘመን - ወለድ ልማድ!
ችሎቱስ ተሰይሟል! ወቅቱን ተመስሎ
ያ - የሽምብራ ጥላው ሥር ፍርድ ውሎ!!

ጥር - 1989 ዓ.ም.
መልካ ሰዲ (መካከለኛው አዋሽ)

* ጋሽ አሰፋው ኃይሉ (እፎየው!)
ካለመታከት! ተስፋ በተመላ ሞራልህ ስላበረታታኸኝ
ማስታወሻ ስጦታዬ ትሁንህ።

## የምኞት ዓለም

እንዲህ - ቅጥ አምባሬ በጠፋ!
በሸፍጥ ዓለም - ምድር ሳለሁ
ተላወሰ እንጂ በድኔ - ለፋ!
እኔስ ከቶም አልደፍር! ለማለት ኑሬአለሁ።
የነፍሴን ነገር ደሞ እንጃ!?
በሥጋዬስ ጉድፌአለሁ።
(እርሜንስ በልቼዋለሁ።)
መቼም! ጠግቦም አያውቅ ልብ
ደርሶም አየሁ! አይልም ሆድ፤
ሰው በሃሳብ ሲግለበለብ
በአበቅየለሽ! ምኞት መንገድ።

ሰኔ - 1990 ዓ.ም.
ሐረር



## ለራስ ነው ማልቀስ!

ለሰዎች ድንጉጥ፣ ትሁት ሰብዓዊ
ምናበ - ሠፊ፣ ምጡቅ! ሕላዊ፤
ብሩህ ዓላሚ - ትጉህ ታታሪ!
ውበት አድናቂ፣ ፍጥረት መርማሪ።
ዕውቀት ናፋቂ፣ ምሮ አስተማሪ።
ቅንነት ለዛ - ባሕርይ ግብሩ
ጥበብ ሞልቶበት - ባፈጣጠሩ!
ጅምር ዕቅዱ፣ ካሰበው ሳይደርስ
ልዩ ሰው! ሲቀጭ፣ አካሉ ሲፈርስ፤
አንድም ለሀገር፣ አንድም ለወገን
ለራስ ነው ማልቀስ!

ህዳር - 1991 ዓ.ም.
መልካ ሰዲ (መካከለኛው አዋሽ)

**መታሰቢያነቷ፡-** በተለይ ሁለ_ገብ ወጣት የጥበብ ሰው ለነበረው ለመምህር አበራ ንጉሤ አደራ (ከ19? - 1991ዓ.ም) እንዲሁም እንደ ሰሎሞን አንለይ(ከ19? - 2004ዓ.ም) ላሉት በአጭር ለተቀጩ ወጣት መስሎቹ ይሁን።

## ፍርጃ!

ከሠፊው አፅናፍ ምህዋራቸው
በጥበብ ፀንተው! ያየናቸው፣
ከዋክብት ረገፉ በተርታ!
በኅብረ - ቀለማት ፈንታ
ጨለማ አይሎ ሊበረታ፡፡
ሕገ - ተፈጥሮ ተዛብታ
ፈሪሃ - እግዚአብሔር ከታጣ!
እንግዲህ መጪውን ማን ያውቃል?
ዘመን ተሻግሮ - ቀን ሲጐድል፣
ወዮላት! ደሞ - ይህች ፀሐይ?
ይዛቡቱባት!
ያሚርቱባት! የለም ወይ?!

ጥር - 1993 ዓ.ም
መልካ ሰዲ (መካከለኛው አዋሽ)

**መታሰቢያነቱ፡-** በየሙያ ዘርፉ ዘመን አይሽሬ
ሥራዎቻቸውን ትተውልን ላለፉት
ለሃገራችን የጥበብ ሰዎች ሁሉ ይሁን፡፡

## የሚመካ!

አንዳች ሳይታበይ! ሰው በሰውነቱ
በዕብሪት ሳይታጐል! ሳይከዳው ጉልበቱ፣
የመልካም ሥራና፣ የመልካም ምኞቱ
ፍሬው እንዲባረክ፣ እንዲሰምር ሕይወቱ!
ኑሮው እንዲቀደስ፣ ጥረቱ እንዲሳካ
ከቶ - የሚመካ!
በእግዚአብሔር ይመካ!!!

ሰኔ - 1999 ዓ.ም
ደበረ - ዘይት (ቢሾፍቱ)



## የዘመን ሞገሶች

በተሰጥዖ! ለብዙሃን ተፈጥረህ
ለአዕላፍ! ፍቅር - ደስታ በመኖርህ፣
እነሆ ... ከነፀብራቅ መሀል ፈክተህ!
እንደአጥቢያ ኮከብ የደመቅህ!!
እፁብ ድንቅ! የጥበብ - ውበት ልሣን
ጥዑም! የሕይወት - ለዛ ድርሳን
እንደቅመማት - የረቀቅህ!!
ከችሎታም በላይ! የላቅህ፡፡
«ታዲያስ ጃል! ...
በማን ዘመን ነው የኖርክ!?» በሚል፣
ቢጠይቁ - ሙታን፣ ወይንም «ሕያዋን»
አ! ... እንዴት ማራኪና፣ አስደሳች ነፍስን!
አኩሪ ነው ምላሹ! የሚያስተማምን፡፡
በዘመን ሞገሶች! ... በእነጥላሁን!!

ሚያዝያ - 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**መታሰቢያነቱ፡-** እንደዕንቁ ፈርጥ እጅግ ብርቅዬና
ተወዳጅ ለሆነው ከቶም ወደር
ለማይገኝለት የሙዚቃ ሰው -
ጥላሁን ገሠሠ፡፡

## ወዳጄን አጣኋት!

በየደረስኩበት፣ የእጄን የሚያሳጣኝ!
ሰው ማመን ምሴ ነው! እኔማ ምን ገደኝ?
ከዕለታት አንድ ቀን፣ ደሞ እንደልማዴ
ተግባባሁ ከአንድዋ ጋር፣ ዘለቃ ገባች ሆዴ::
ዳግመኛ ፈታ አለ፣ ልቤ ተላላው
አሣሩን እያየ! እማይማረው::
እናም ውሎ አድሮ፣ ቀን አልፎ ሲመጣ
ከነፈ ፍቅራችን! ማረፊያ እስከሚያጣ::
እጅና ጓንት ሁነን፣ ስንኖር ለዓመታት
ተላመደች ቤቴን፣ ከቶም ባሌ ዐወቃት!
እህል ውሃ አለቀ! ተበጠሰች ማተብ!
እኔንም እንዳሻኝ ከእርሷው ጋር ይጣገብ::
ሁሉም ይቅር ሌላው፣ በአፍንጫዬ ይውጣ!
ግን ገሃነም ይግባ! በክብሬ የመጣ::

የካቲት - 2002 ዓ.ም.
አዲስ አበባ



## ጊዜ

የጊዜ እሽቅድድም፣ ድሪያ ተካቶበት
ትናንት ሆነ ዛሬ! ቅዕበት ተመላበት
እርጋታ እንደሁ የለ - ሁካታ እጐላበት።
የታገሰ ቀና፣ በማስተዋል ሰክኖ
ፍሬ - ዐልባ ተዛባ፣ ፅናት ባጣ ባዝኖ።
የጊዜ መዘውር፣ በቀመር ሲለካ
ድሮ ለዘንድሮ፣ ዕለት - ነግ ሲተካ፤
ሕይወት ሳይጠገብ - አንዳች ሳያረካ!
ወትሮ ዘለዓለም'ን፣ በከንቱ እያስመኘ!!
መሰንበት ከርሞ ሰው፣ ዘመናት ይዘልቃል
የነበረ ኹነት - በሽረት ይታገማል።
አይ! .... ጊዜ?
ቅብጥ-ብጥ አባዜ!
ፍርጃ - ለባለጊዜ! ... አጥቢያው ለደረሰ
ሕግጋት ታድሞ፣ ክፋትን በታዘዘ።
በገነነ ዝና፣ ዓውድ እየናወዘ
ሲደጋግዘ - ቀኑ! ቆይታን ተከዘ።
እልፊያ ይቅዘፍ ባሕር (ጎዋ) - እየተንሳፈፈ
መንፈት ከእምባ አይቀርም - ምኑን ተተረፈ?!

ሚያዚያ - 1979 ዓ.ም.
ሐረር (መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም)

## ሰው

«እንደዓመል - እንዳመሉ
ካፈጣጠር ይሰያል» ይላሉ።
የባሕርያት አባት
ሊቀ - ሊቃውንት፣
ሰለ ሰው
ሥነ - ልቡናው
እንደየሰብ - አግባቡ
በጥልቅ፣ በስፋት ሲጠበቡ።
ቃዲያን . . . እነሆ ሰው!
ዙሮ ዙሮ ዙሮ - ያው፤
ፍላጐቱ! . . .
ክልስ - ብርዝ
አሁንም አሁንም ዕዝ!
ለራስ በራስ
እስከመቼም ግብዝ!!
ፊቱ . . .
የየስሜቱ . . . ልውጥ መቅድም
የውስጥ ፈውስ፣ የውስጥ ሕመም።
በአብዛኛ . . . ዓመለኛ
ያውም - ግለኛ!
ይግረም ሲል ደሞ ለክፋቱ!
ከሁሉ ሁሉ አድራጐቱ
ብርቱ ጉልበቱ፣ ብልጣ - ብልጥነቱ!
የሰው ነገር - መዘመኑ!
እርሱውን እንኳ እራሱኑ
አስታዋሽ ያለመሆኑ።
ኧረ - ምኑ?
ኧረ - ስንቱ?!
እንዲያው - ሰው! በሰውነቱ
ሌላውን ሁኖ - አለማየቱ!!

ኅዳር - 1984 ዓ.ም.
ሀሰበ - ተፈሪ (ጭሮ)



## ጀበና ግዘፈቱ!

ጀበናው - ትልቅ ጀበና!
ፈሳሽ የተከለሰ - ውስጡን ቡና፣
ፍሬው ሁላ
እያረረ የተቆላ!
ተወቅጦ - ደቆ
ከፍልቅልቁ ውሃ ተደበላልቆ፤
ኪያ . . . ግዙፍ ጀበና!
ካናቱ - ትንሹ፣ ሆዱ - ሰፊው ሸክላ
ፍም ግማድ ጥዶቱን!
ውዜት -'ጭምሬቱን የፈላ።
ተዋውጦ ቅልምቱን፣ ከፅልመተ - ጥላ
ዱቂት ከፍሰት - እንፋሎትነት የተብላላ!
የምድጃው ቆሌ፤ ትልቁ ጀበና
ፈሳሽ የተከለሰ - ውስጡን ቡና፤
ፍሬው ሁላ
እያረረ የተቆላ!
ቁሌቱ የደበነ
ውቅጫው የቦነነ!
ፍላቱ ... እያለፈ - እያረፈ
በጭውውቱ ... እያስማማ - እያወራረፈ
ጋል በረደ. - የተንተፈተፈ!
እየተንተከተከ - የተንፈቀፈቀ
እየተንፈቀፈቀ - የተንደቀደቀ::

እየተንሰረሰረ - የሰከነ
እየሰከነ - የተንሰረሰረ!
ኃያሉ ጀበና እንደተከደነ
ግዝፈተ - አድባራቱን የተካነ፤
ከተመ!
አገር፣ ምድር ሥፍሩን ሆነ!
ከመከተሚያው ኋላ
ፍፃሜ ቅሪቱ - ያው ዝቃጭ አተላ።

ሚያዚያ - 1984 ዓ.ም.
መኢሶ - በምሽት ባቡር ጉዞ መስመር ላይ.

* ተስፋ ለራቃት ምድር
- ወዳጄ ሽመልስ ሹምዬ አድናቆትህና አገዛህ መቼም አይረሳኝ።



## ሞት - አይወደድም፣ አይፈራም!

ሰውን ያህል ክቡር! አምሣያውን ፍጥረት?
ያውም ቅን አሳቢ! ተጠባቢን መትዳት
በሰበብ አስባቡ - ማሰር ማንገላታት
በደባ ማስቅየት - ዓይን ዓይኑን ማጥፋት!
በግፍ! መግደል - መፍጀት!?
ፍርሃት ጭካኔ እንጂ! ወንጀል ጀብደኝነት
ድንቁርና! ሽፍጥ እንጂ! እብሪት ፍፁም እብደት!
ጉብዝና እኮ አይሆንም - አይደለም ጀግንነት።
እኩይ! ምግባር እንጂ - ግዙፍ አሣር ኃጢያት!
እርጉም ውጉዝ ሥራ! የእርኩሰት ድርጊት።
ግና . . . ገድሎ ከሚያለቅሰው?
ሞቶ ለሚያኖረው!
ለጉብዝ! ሰውማ
ለጀግኖች - ጀግናማ!
ለመልካም ሠሪ! ግርማም
ለሩቅ ዓላሚው ዓይናም!
ለምሁር! ሰውማ
ለሊቆች - ሊቅማ!
ለመልካም ጠቢብ! ልባም
ለሩቅ አሳቢው ሕልማም!
ሞት - ከቶ አይወደድም
ሞት - ከቶም አይፈራም!!
እንዴት ቢባል ለምን?
የመለየት ቅጣት - መሪር ሕማማትን!
ሰብዓዊ ርኅራኄው - ስለሚያመዛዝን።
ምንኛ ቢገዝፉም! ላቅ ባለ ዝና!
ማለፍ እንደማይቀር! ጠንቅቆ ያውቃልና።

ጥር - 1989 ዓ.ም.
መልካ ሰዲ (መካከለኛው አዋሽ)

መታሰቢያነቱ፡- ለአሰፋ ማሩ በጊዜው እንዲሁም ለመሰሎቹ ሁሉ ይሁን።

## ግራ ወዳጅነት - ግራ ደመኝነት!

አንቺና አፍቃሪሽ! መንታ ገፅ አላችሁ
እስከወዲያኛችሁ - እሚያዋህዳችሁ!
በልዩ ቁርኝት፣ በተቃርኖ ልምዶች
የተጣመራችሁ! የቃል - ኪዳን ጥንዶች
ሌት ተቀን ወዳጆች፣ ሌት ተቀን ደመኞች::
ያንቺና ወዳጅሽ፣ ግራ ባህርያት
ፍቅራችሁ የጠና - እስከመጠፋፋት!
እንዲህ ነው መዋደድ! እንዲ እንጂ ነው ፍቅር!
ሳይለያይ አኑሮ፣ ሳይነጥል የሚቀብር::
አንቺና ምርኮኛሽ - የውላችሁ ፅናት!
መስተፋቅራችሁ፣ ኃይለ - ምሉዕ ምትሃት!!
ዕለት - ተለት! ካለመታከት
እዚም እዛም - መጓተት!
ዳበስ፣ ዳበስ - እሸት! ደሞ አየት፣
ሳብ - ሳም፣ ሳብ - ሳም
በውህድ ጠረን - ዐልቦ መጣጣም!
ለደስታ - ለኃዘን፣ ደግሞም ለትካዜ
ደራሽ መሣይ ሽሪክ - የሙጥኝ አባዜ!
በልዩ ቁርኝት፣ በተቃርኖ ልምዶች
የተሳሰራችሁ! የቃል - ኪዳን ጥንዶች
ሌት ተቀን ወዳጆች፣ ሌት ተቀን ደመኞች::
እንዲ እንጂ ነው ጥምረት! እንዲህ ነው መዋሃድ!
ሳይለያይ አኑሮ፣ ሳይነጥል የሚያነጉድ::
ግና ... የፍቅራችሁን ልክ! ከግምት አካተን
በንፅፅር መንገድ - ግራ ቀኙን አይተን፣
እውነታው ካግባባን፣ ሳይኖረን ቅያሜ
በቅን ልቡናችን፣ ብንሰጥ ድምዳሜ፣
እነሆ! አንቺና ወዳጅሽ - እስከፍፃሜያችሁ!
አለው ትርጓሜ - ግሩም ዝምድናችሁ::



ባንድ ወገንሽ የዋህ! ባንድ ወገንሽ እሣት!
አንዱ አንዱን ለማበነን፣ አንዱ አንዱን ለመፍጀት
እልህ ተያይዘው - እስከመጠፋፋት!
ካለመስተጓጐል ... እሚሳሳቡበት::
ካለመሰላቸት! ... እሚጓተቱበት
ግራ ወዳጅነት - ግራ ደመኝነት!
የልክፍት አዙሪት! ... እንቅቅልሽ ዑደት::
ከምርኮኛሽ ጋራ! «ከጀለስሽ» ጋራ!
አቦ ... እንዴት ነሽ ሲጋራ!?

ሰኔ 1999 ዓ.ም.
ደብረ - ዘይት (ቢሾፍቱ)

እሩጥ! ... አታንጋጥ - ሩጥ!
እሰየው! የኛ ልጅ፤ ጀቢራው የዓለም ፈርጥ
እንዲህ ነው መቅደም! እንዲህ ነው መብለጥ!
ስመ - ጥር ጀግና! ከምርጦች በላይ ምርጥ!!

ሚያዚያ - 2003 ዓ.ም.
ደብረ - ዘይት (ቢሾፍቱ)

መታሰቢያነቱ፡- በዘርፉ እጅጉን ለላቀ ታላላቅ ድሎች ፋና - ወጊ
ለሆነው ለጀግናው አበበ ቢቂላ ይሁን፡፡
እንዲሁም ድሉን በጀግንነት ላስቀጠሉት
አንጋፋና ወጣት ብርቅዬ አትሌቶቻችን
በሙሉ ስለአርዓያነታቸው ማስታወሻ፡፡



## ሕልም አለኝ!

ርቆ መፈጠርን፣ ከሃገር ልማድ ባህል
አጉል ነገር! እያልኩ - ስተች ሳብጠለጥል፤
ለካስ ለበጐ ነው!
ሕልሜን በአንተ ላየው?
ከአያሌ ማይሎች - ድንገት ከተፍ ያልከው!
ገና በጨቅላ ዕድሜ - አራትም ሳይሞላህ
ኢትዮጵያን የማየት፣ ዕድሉ ቢገጥምህ፤
ምኑ ገብቶህ ይሆን? እንዲያ ተመስጠህ!
እንደዐዋቂ ሁሉ፣ ከልጅም ወግ አልፈህ
በንፁህ ልቡና፣ በንፁህ ፍቅርህ
በፈረንጅ አማርኛ - ጣፋጭ አንደበትህ!
ፀጋ - ተፈጥሮዋን፣ መውደድህ - ማድነቅህ!?
እናት ምድርህን፣ ትውልድ ሐረግህን
እንግዳ ተቀባይ - ትጉት ወገንህን፤
በማወቅህ ደስታ - በመረዳት ብቃት
በሚያስደምም ስሜት - የዜግነት ኩራት!
ያገር ውብነቷን! የዓየሯን መመቸት
በንፅፅር ዘዬ - አዋደህ! ስትገልፃት
ሁኖብኝ ዱብዳ! ሆኖብኝ ተዓምራት!
ከመገረም በላይ! ሕልሜን ባንተ አየሁት፡፡
የቃል - ኪዳን ምድር፣ በተስፋው ያሰባት
ኢትዮጵያ ናትና! የሰው ልጆች እናት
ትንቢቱ ሊፈፀም - ቃል የተገባላት!
ፈቃዱ ሲሞላ፣ በዓምላክ ስትባረክ
በአንተ አምሣል - በአንተ ልክ!
ሺህዎች ሲፈጠሩ! ከወገኖች አብራክ፡፡
በአዲስ ትውልድ እርካብ - ላዲስ ዘመን ብሥራት!
እግዜር በትንሣኤው - ሃገሬን ሲቃኛት
ሕልም አለኝ! ስለእውነት
በአምሣዮችህ እና በአንተ ውስጥ ያየሁት፡፡

እንደ መሀቡባ፣ እንደ እነ ፑሽኪን
እንደነ ኤዞፕ ሁሉ - ማንነት ተነጥቀን?
እንደማንቀር መና! እናንተን ተስፋ አርገን::

ሚያዝያ - 2003 ዓ.ም.
ደብረ - ዘይት (ቢሾፍቱ)

**ማስታወሻ ስጦታዬ:-** ቶሮንቶ - ካናዳ እና በአሜሪካ ምድር ተወልዳችሁ
ለምትኖሩት እጅግ በጣም ብሩህ እና ተፈቃሪ
ተሰጥዖ ለተቸራችሁ
1. ለልጅ ዓማኑኤል ጌትነት (ዓማን)
2. ለሕፃን ቤተልሔም ምስክር (ቤቲ)
3. ለልጅ ጆሴፍ ዮሐንስ (ጆሲ)
እንዲሁም ለመሰሎቻችሁ ሁሉ ይሁንልኝ::



# ያንዴ ፈረቃ

አሃዱ ብዬ ስገለጥ
ከእናቴ!
ከማኅፀን ቤቴ
ስወጣ፤
በእሪታ ጩኸቴ
በልቅሶ ምሬቴ!
ወደ ዓለም ስመጣ፤
ምናልባት!
ላንዴ ሕይወት ፈረቃ
ምልድ - ፍጥረቃ!
ሠረቃ! ... ሲቃ!
እርሷም - ምድሯ
የወግ ብራ!
ዝፍት አረዳ
ኪራዮ - ምንዳ!
ቀለመ - መዓት! እያሌ
ዝንጉርጉር ቡራቡሬ፤
ከቀዬዋ ዐቅም እንኳ ካፀዱ
ዑዳሉ
ነቁጥ ነጠብጣብ፣ ግተ - ሙሉ::
የደመቀባት ግልግሉ!
እኔም - እንግዳው

ለዚያችው!
ላፍታ ታህልዋ ቆይታዬ
ያውም ላንዴ፣ ብቸኛ ፈረቃዬ!
የንጓሁ በምኞት፣ ቀቢፀ - ተስፋዬ::
ደግሞ ያኛው!
ማለት ፈረቃው
ያው ያንዴው!
ቀድሞውኑ የታደመ
ቀና 'ይል ከዘመመ፤
ከጅምሩም ታምቆ የታሸ!
ኑሮ የለሸሸ፤

ይግረም ሲል፣ በእርሱው ብሶ
ተቻኮለ!
መሳልሶ! ... አይሆኑ እየነሆለለ።
እንድያ እንዲያ ባለ ጥድፊያ
ፈጣን ክርሞ፥ ፍፁም ክንፊያ፥
አጅሬ!
አይቀሬው ተካነፌ
በቅፅበቱ እየዳሰ መረሸ!
ላይን ያዘ መሻሽ
አንዴው - የታበየው!
ጭርሱን አይሆኑ የተበለሻሸ።

*   *   *

በይ ደህና ሁኚ ጀምበር!
ቸር ስንበች ጨረቃ!
ላንዴ ሕይወት ፈረቃ
ቀን አልቆ - ዘመን ሲያበቃ፥
እንግዲህ ዘራዳም፣ ምን ይሆን ብልሃቱ?
ለማይቀረው ዕዳ!
ለማለፊያ - ማረፊያው ስንብቱ!?

ጥቅምት - 1984 ዓ.ም.
ገለምሶ (ሐብሮ)

መታሰቢያነቱ፡- አጅግ ለማደንቅሽ ገጣሚ ፈርማዬ ዓለሙ ይሁንልኝ። «ይህንን እና ለራስ ነው ማልቀስ! የሚለውን ግጥምህን ደጋግሜ እያነበብኩ ሉቱን ሙሉ አስለቀስከኝ።» ባልሽኝ ስድስት ወራት ሳይሞላሽ ሳንገናኝ ማለፍሽ ለቀቀን ሁኖብኛልና - አንቺን ይዘክርልኝ።



## ንጣት ሲኾርጉረጉር! ሲጠቆር

አይበጅ!
እርሱስ መች ይበጃል?
በተግሳፅ ቃል
<እንዲህ እነጂ!> ሲባል፥
ምን ያድርግ?
እርሱስ ምን ያድርግ ጃል!?
ዋ! ... ምን ያድርግ?
<በሕግ!> እያሉ በሕግ
ሕቅ!
<ዋ!> .... ሙሉ ሙሉ
ያቀረቡለትን ቢጋት ቢምግ፥
አይፈረድበትማ!
ስለ ሐቅ - አይፈረድበትም!
ዳሩ የሆነውንም ቢሆንም።
መቼስ እምቢ አይል ነገር
እምቢኝ! አይል
እ? አይሸፍት አያብል፥
አካኪ - ዘራፍ! ደርሶ ጥል
ቅጥ እማጣት አቅል።
አይጣል!
እንግዲያማ ምን ይበል?
ምንስ ይል?!
ያለውል! ...
እንዳረግ - እንዳረጉት ከመቀበል።
አሄሄ! ... ወረቀት
እንጃለት - ፈርዶበት!
ያ ... ንፁህ! ንፁህ
ባለዳዴው፣ ድኽ - ድኽ፥
ስስ፣ ፀአዳ፣ ነጩ!
ግልፅ፣ ግልፅ - ግላጩ
ግልብጥባጩ!
ባዶ፣ ባዶ - ባዶው
ነዶ፣ ነዶ - ነዶው!
ሉኽ ንጣት ወረቀቱ

ነፍሱ እንደሁ ጠፍቶም በቁመቱ!
በእንጭለት፣
እንጭጭነት፣ እንቢኤትነት - ዛፍነቱ!
አገልግሎት መጠለያ፣ ቅርስ - ሲሳይ፣ ጌጥነቱ፡፡
ዋ! ... መጥኔ!
እንዲያ በጭካኔ!
ሲጠቆር፣ ሲኾጉረጉር
ሲጫር ሲሞጫጨር!
ደም - እየቻለ በቻለው!
እንግዲህ እርሱስ፤
ከመያዝ ወዲያ፣ ምን ይሁነው?
የሰጡትን - እንዲያቀልመው፡፡
በውነቱ! ... ወረቀቱ
ታፍጐ - ተንፍጐም ከመቅረቱ
ኧረ .... ከምን ሳይ ሁኖ ያሆን ጥፋቱ!?
ዳገሚያ ... እንዲያ!
በዱልዱም ባሳቻም ጣት ዕጣ
አልባሌ ኾሰጣ!
ኧረ .... በስንቱ
ስይሆኑ መቀጣቱ?
ከንቱ ምታት መመታቱ
ባይሞቱስ ሞት መሞተቱ!?

ጥር - 1984 ዓ.ም.
አሰበ - ተፈሪ (ጭሮ)

መታሰቢያነቱ፡- ለኢትዮጵያ ተማሪዎች እና ምሁራን ንቅናቄዎች ይሁን፡፡



## የቁራ ጩኸት!

«እባክህን ጌታው! የእግዜር ታናሽ ወንድም
የዛሬን ማርልኝ - ሁለተኛ አልወልድም!... »
ድፍን ልብ አይራራ፣ ወገኖች ተጉዱ
ደም እንደተጠማ! እየተራረዱ፡፡
እንደጭዳ ግብር፣ ትውልድ እያለቀ!
እናት በምሀላ! ማኅፀኗ ደረቀ፡፡
ዋ! . . . . . . . . . .
ይድረስ ለክብርት እህቴ!
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ!
ገና በለጋ ዕድሜ፤
ሳይደርስ ዓለማችሁ - ሳይሞላ ፅዋችሁ!
በጅምላ ጭፍጨፋ! በግፍ ላለቃችሁ፡፡
ኧረ - ምን ነበረ? ሕልም ራዕያችሁ!
ሳትሳሱ! ያስከፈለ - እንደጨከናችሁ
ያንዱዋን ፈረቃ! ውዷን ሕይወታችሁ!?

* * *

በየአደባባዩ! በየጉዳናው ላይ
በጠራራ ፀሐይ
እንደ አራዊት ሲሳይ
ስትውሉ - ለግዳይ!
ንፁህ ደምህ! ሲፈስ
ሲረጭ - ንፁህ ደምሽ!
የወገን ያለህ! ... ባይ
ካገር ጠፍቶ ደራሽ!!
እግዚኦ! ... ዋ'ኔ!ዋ'ኔ!መጥኔ!
እንዲያ በጭካኔ!
ኡሉሄ! . . . . . ኡሉሄ
እህቴ - ወንድሜ፤
እንዴት ነበር ያኔ!?
ምን ነበር ሕመምሽ?

ምን ነበር ስሜትህ?
ሲራኮቱ! በመከራህ
ሲጨክኑ! በስቃይህ፤
ስትፈርጅባት! በቀንዲልሽ
ስትፈርድባት! በፀሐይህ!?
ያንት ያለህ!! ቷ

* * *

አቅጣጫው ከማይለይ
ከምድረ - በዳው ላይ
በበረሃ - ስደት!
ድካምና እንክርት፤
ተሟጦ! አቅማችሁ
ተሰብሮ - ቅስማችሁ!
ስትሆኑ ለአውሬ ራት
ለነፈዝ ጨዋታ! ለሽፍታ ፍላጐት::
አቤት! . . .
ኧረ - ለምን ነበር ትግልሽ?
ለምን ነበር ትግልህ?
ለማን ነበር ሞትሽ!?
ለማን ነበር ሞትህ?
አበሣ ስቃይሽ!
እንግልት እሣርህ!?
መስዋዕትነትሽ! መስዋዕትነትህ!
ድርብ ኃዘን! ሁኖን
የእግር እሣት! ሁኖን
ምንኛ ቢጠብሰን!?
ምን ቢያንገበግበን!!
መቼስ፤
ቀሪን ለመታዘብ - ዕድል ስለሰጠን!
በትግላችሁ! . . . «ትግል» እያየን
በሞታችሁ! . . . ሞትን! እያየን
እኛስ ይኼው - አለን! . . . አለን
ድንገት ቢሆንልን! መኖርን ፈልገን::



አ! ... ለጉድ - የፈጠረን !!!
ለእርግማን! ያቆየን
ለእሣር! ያስቀመጠን::
(ለዕዳ የጐለተን::)

መስከረም - 2001 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

መታሰቢያነቱ፡- ለዚያ ትውልድ ይሁን::

## « የውጭ አልጋ . . . »

ከኤደን ጣራ፣ ከገነት እምብርት
ፈልቀህ - መንጭተህ፣ ከዘመን በፊት!
ከፑንት እስከ ኑቢያ - ምሥር
የጥንተ - ሥልጣኔው አድባር!
በንዳድ በረሃ፣ ጭንጫ መሬት ስታረሰርስ
በቀትር ወበቅ፣ የስፊኒክስን አንጀት ስታርስ!
በአስዋን ጠለልህ፣ ሁነህ የአሌክሳንደሪያ ሞገስ
ለብርቅዬ ፒራሚዶቹ ድንቅ ውበት! ስትለግስ
የአያሌ ትውልዶች ሕይወት! ስታቀፅል - ስታድስ፡፡
«ኢጂኘት - የዓባይ ስጦታ! » እስክታሰኝ
በታላላቅ አድናቆታት ስትናኝ!
ከተትረፈረፈው! ፀጋ በረከትህ
አንዳች ሳትፈይድ! ለወላድ መካን ምድርህ፣
የወንዜ ልጅነትን፣ ኀብረ - ነገር ንቀህ
ከዘመን ዘመን ስትጐርፍ፣ በቁጣህ ገንፍለህ!
ከሸለቆህ አብራክ፣
እንደፈጠረህ! የፈጠራቸውን ነፍስያት - በልክ!
የበይ ተመልካች - ተመፅዋች! እያደረክ
ምነው ጊዮን? ምነው ዓባይ?!
ከሁሉ በታች ያሳነስክ?!

* * *

ቢሄዱ ከማይጨርሱት! ምቹ መስኮች መሀል
ካላጣሽው ሁዳድ - ካልጠፋ ጠለል
ወደህ - በገባሽው ገደል!!
የጠቀምክ ይመስል - የበጀህ ይመስል?
ዓባይ ማደሪያ አጣህ እስክትባል!
ስታፈዘን በተረትህ
ስታስጨፍር በዘፈንህ፣
ስንቱን ትውልድ አቂለኸል?!
ስንቱን ዘመን? አማለህ አልፈኸል፡፡
ወየው! ዛሬስ - ጉድህ ፈልቷል!
እንግዲህ ዓባይ . . . . ዕዳህን ቻል፡፡



* * *

የውጭ አልጋ!
የቤት ውስጥ ቀጋ! እንዲባል፣
እልፍ አዕላፍ ዘመናት!
እየጐረፍክ - ስታማልል
እየዘፈፍክ - ስትመዘብር!
በንፍገት - በበደል ኑረኸል፡፡
ከዘ - ፍጥረት እስከ ህልፈት
ደሞ ስንቱ ይታገስኸል?!
ይኼው ዛሬ! . . . ጊዜው ረፍዶ ለቁጭት!
ባለፍክ - ባገደምክበት! በየደረስክበት
ጠያቂህ እንደአሸን ፈልቷል!
ሀገር ሊሞግትህ! ሊፋረድህ ዝቷል!!
ትዕግስቱን ብታሟጥጠው
እልሁን ብታስጨርሰው!
የመጣው ይምጣ እንጂ! ወገን ቆርጦ ተነስቷል!!
ለዘመናት ብክነት! ተጠየቅ ብሎኸል፡፡
እንጃልህ - ዘንድሮስ! ጊዮን ጉድህ ፈልቷል!
ሳያጡ ለማጣት - ተወቃሽ ሁነኸል፡፡
ለንፍገትህ - ንፍገት፣ ለበደልህ - በደል!
እንግዲህ ዓባይ - ዕዳህን ቻል፡፡
በል ዓባዬ . . . . . ዕዳህን ቻል!!

ነሐሴ - 2003 ዓ.ም.
ደብረ - ዘይት (ቢሾፍቱ)

እምብዛም አይርቁ - እጅግ ተንሠራፍተው!
በየአቅራቢያችን - በየውስጣችን! ነውና አድራሻቸው::

ግንቦት - 2003 ዓ.ም.
ደብረ - ዘይት (ቢሾፍቱ)

**መታሰቢያነቱ፡-** ለመከረኞቹ ዜጎች ሁሉ ይሁን::

**ማስታወሻነቱ ደግሞ፡-**

*ለአክስቴ ልጅ - ለወንድማዊ ታምራት አራርሶ (ማሙሽ) ይሁንልኝ:: እውነታውን በአካል ስለሚያውቀው - ይህ ግጥም ጥሩ ገላጭ እንዲሆን በመነሻት ምራሉን አጋርቶኛልና::



## ያ - ጥቁር ግሥላ!
(ቁጥር - 1)

«እንደ ተላላ ነፍስ፣ ግብዝ ሰው ይመስል
እንደ ሁሉ ብርቁ! ልቡ እንደሚማልል፤
ሎንዶንና ፓሪስ - ኒውዮርክንም ያህል
በክብር ጠራኸ - ጉብኝልን ከምባል?
ከቅያሜም አይደል፣ ልንገራችሁ ከእውነት
ደጋግሜ አስሬ! ኢትዮጵያን ብቃኛት፤
ከምንም ነገር በላይ! ነፍሴን በማስደሰት
ሕይወቴን የሚያድስ፣ የሚሰጠኝ ሐሴት
ግርማ ሞገሴ ነው - ለእኔ ታላቅ ኩራት!»
ወጥት የማይሰብር፣ ውስታ እማይከላ
የነፃነት ሉሌው! ያ - ጥቁር ግሥላ
እውነትን የኖራት ... እንዲህ ነው ማንጼላ!!

* * *

ለአርትፊሴል ነገር! ለሚብለጨለጨው
እንደጤዛ ሰፍር፣ በኖ ለሚረግፈው
«እፍ!» ያለበት ለታ - ለሚንኮታኮተው!
እንደተላላ ሰው፤
መች ተረታች ነፍሱ?!
እናት ጓዳው ድርሱ
ኢትዮጵያ ነች ለእርሱ::
የክፉ ቀን ግርግም! መጠለያ ዳሱ
ምስጢረ - ቋቱና ገመና አመሳሱ::
ከፍቅሯ ተጣብቶ፣ ለምልሞ መንፈሱ
እንዳልባዘ ጠረኗ - ተዋዶ ከነፍሱ!
ያመሰካት ምድር! የቃል - ኪዳን ቅርሱ
ፈጣሪ የባረካት! ቤተ - መቅደሱ::
ኢትዮጵያ ናት ለእርሱ. . .
የሃገራት ቁንጮ - ተምሣሌት ሞገሱ!

* * *

ሃገሬ ውቢቱ!!
የፊካ ታሪኩ! ያ - ብርቅዬ ሰሙ
ከገናኖች ተርታ! ከታላላቅ ደሙ
እየናኘ ዝናው! - ለትውልዶች ግዘሙ
ሕያው ሁኖ እንዲኖር ... እስከዘለዓለሙ!!
እምዬ ኢትዮጵያ! የታሪኩ አለኝታ
በብዙ ደክማለች - በዓምላክ ፀኑ እርዳታ!
የነፃነት ቀንዲል! ... ሻማ ሁና በርታ::

* * *

ካረገችው ሁሉ - አያሌ ውለታት
እርሱስ ቢሆን ከቶ! ጀግናው መች ዘነጋት?
ከሃገራት ሁሉ - እጅጉን አልቋት!
በርቱዕ አንደበቱ! እያቆላጸላት፤
«ስምሽን አንስቼ - አልጠግብሽም!»አላት::
እስከወዲያኛውም!... ክብሯን አውጆላት
«ቅድስቲቱ ምድር - ኢትዮጵያ ብቻ ናት!»
ሲል መሰከረላት::

* * *

መላልሶ እንደሰራይ፣ ደጋግሞ እንደመተት
የተጠጋት ደዌ! የተጣባት ገተት፤
እንዲያ ... ስጋዋን ጨርሶ - ባጥንቷ እያስኬዳት!
ይሉኝታ - ቢስ ሽሏ! ማፈሪያ ሲያፍርባት::
እውነትን የሞራት! . . .
ወጭት የማይሰብረው፣ ውለታ አማይከላ
የነፃነት ሞገስ! ያ - ጥቁር ግሥላ
ሃገሬን የሚያያት!
ኢትዮጵያን የሚያውቃት!... እንዲህ ነው ማንዴላ::

ኅዳር - 2006 ዓ.ም
አዲስ አበባ

**ልዩ መታሰቢያነቱ፡-** ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይሁን - ጃንሆይ!
**ማስታወሻነቱ ደግሞ፡-** ለአክስቴ ሙሉእመቤት ገ/ዮሐንስ ወ/ማርያም
ይሁንልኝ::
ምክንያት - ሁልጊዜም የማስተውለው የሃገር ፍቅር
ስሜቷ (ሃገር ወዳድነቷ) ስለሚያስደንቀኝ::

Design by Tsion Gelachew

Price $25

አለሙ የምስራች በለጠ እና ጓደኞቻቸው የህትመትና ኦዲዮቪዥዋል የሽርክና ማህበር